# መደመር ከማን ጋር?

መ ርምሮ አካሄድን ርምጃ ሳይወስዱ

ደ ፋ ቀና ቢባል በፍቅር ቢነዱ

መ ረቡን ዘርግቶ መርዙን እየረጨ

ር ካሽ ትርክቱን ሞኝ እያስጎነጨ

ከ ፋፍሎ የሚበላው የቀን ጅብ ሳይጠፋ

ማ ን ከማን ይደመር ለምንስ እንልፋ?

ን ፁህንን በግፍ የሚያጠፋው ጠላት

ጋ ሻና ጦር ይዞ አገሬን ሲንጣት

ር ህራሄ ቢሱ ዘርፎ ተደራጅቶ

ነ ውረኞች ተሹመው ፍትህ አፈር በልቶ

ው ህደቱ ጨነቀኝ መደመር ተዝናንቶ።

ዘውዲቱ የማነ

2018-09-07